# ተሸፋፍነው ቢተኙ ገልጦ የሚያይ አምላክ አለ!

ታዛቢው ከለንደን

የቀድሞው አማራጭ ሀይሎች ምክትል ፣ ቀጥሎም የኢዴፓ፣ ከዚያም የቅንጅት ላዕላይ ምክር ቤት አባል፣ አሁን ደግሞ የወይዘሮ ብርቱን ሚደቅሳ ፓርቲ አባል አቶ ክፍሌ ጥግነህ:: ይህ ድርጅት እንደ ሸሚዝ የመቀያየር ልምዳቸው ከሀገራችን ግንባር ቀደም የፖለቲከ ድርጅት ቱሪስቶች ተርታ ሳያሰልፋቸው እንደማይቀር እገምታለሁ:: እኔ እንኳ በአካል ያወቅሁዋቸው ድርጅቱን እንዲህ ቅርጫ ሊገቡበት ቅንጅትን ወክሎ ወደ አውሮፓ የመጣው ልዑክ አባል ሆነው ወደለንደን ብቅ ያሉ ጊዜ ነበር:: በወቅቱም በከተማችን በተደረገው ሕዝባዊ ስብሰባ ላይ መገኘታቸውን አስታውሳለሁ:: ሆኖም ግን ባልታወቀ ሁኔታ ከዕረፍት በኋላ ከተቀመጡበት ወንበር መድረክ ላይ አልታዩም ነበር:: ቡድኑ ወደተለያዩ የአውሮፓ ከተሞች ሲንቀሳቀስም ከሁለት ወይም ከሶስት ቦታዎች በስተቀር አብረው አልሄዱም:: ለምን? ጥያቄውን ለእሳቸው እተወዋለሁ::

ዛሬ ደግሞ ለንደን ይገኛሉ:: ከግም ሞት (ከግንቦት) ሰባት ዋና አስተባባሪ ነን ከሚሉት ግለሰቦች ጋር ብቅ ብቅ ሲሉም ተስተውለዋል:: ጥያቄም አጭሮብኛል:: እሳቸውንም ጥያቄ ምልክት ውስጥ አስገብቷቸዋል::

ምክንያት: በለንደን የሚገኘው የቅንጅት ዩኬ ድጋፍ ድርጅት ለሁለት ተከፍሎ በሁለት የተለያዩ መድረኮች አባላታቸውን ሰብስበው የመለያያ ሰበቦቻቸውን ከገለፁ በኋላ ትክክለኛ ው ማነው? ቀጥሎ ምን ሊመጣ ይችላል? የሚሉትን ዓይነት ጥያቄዎች ለመመለስ ህዝቡ አድፍጦ ሁኔታዎችንና ሂደቶችን በአርምሞ በመመርመር ላይ ይገኛል:: ታዲያ ያጋጣሚ ጉዳይ ሳይሆን አንዳንድ ጠቋሚ ፍንጮች ብቅ ማለት ጀምረዋል:: ለመለያየታቸው ዋና ምክንያቶች ናቸው ተብለው ከቀረቡት አንዱም የግም ሞት (የግንቦት) ሰባት ሊቀመንበር ወይም ፀሐፊ (ስለ ሃላፊነት ምድባቸው እርግጠኛ አይደለሁም) ዶክተር ብርሃኑን በቅንጅት ስም እንጋብዛቸው የሚለው አጀንዳ ተነስቶ ሲያወዛግብ ከቆየ በኋላ የድጋፍ ድርጅቱ ሊቀመንበርና ፀሐፊ ጥለው ይወጣሉ:: ምክንያታቸውም የተሰጠንን የህዝብ አደራ መብላትና የአባላታችንን መብት መጋፋት ስለሚሆን ብርሃኑን በቅንጅት ስም አንጠራም የሚል ጠንካራ አቋም መያዛቸው እንደሆነ ነግረውናል:: ቀሪዎቹ ካልመጣ በማለት አሻፈረን አሉ:: ሁኔታውም ተካረረና ኮሚቴው ለሁለት ተከፈለ:: አፍቃሬ ብርሀኑ ቡድንም የራሱን የቤተሰብ፣ የዘመድ አዝማድና የጓደኛ ስብስብ አመራር ውስጥ አስገብቶ እራሱን አጠናከረ:: የግንቦት መስራቾቹ ብርሃኑና አንዳርጋቸውም በዚሁ ቡድን ለንደን ገብተው ተስተናገዱ:: ስብሰባው እንዳሰቡት አልጋ ባልጋ ሳይሆን በተቃዋሚዎቻቸው አስገዳጅነት የተከራዩት አዳራሽ ስለተዘጋባቸው ተሯሩጠው ሌላ በመከራየት መሰብሰባቸውን ሰምተናል::

የሚያሳዝነው ግን የግም ሞት (የግንቦት) ሰባት መስራች በንግግራቸው ላይ ባለማወቅም ይሁን በንቀት «የትግሬውን አምባገነን መለስ ዜናዊን አውርጄ: የአማራውን አምባገነን ሃይሉ ሻወልን ልተካ ነወይ?!» ሲሉ ተደምጠዋል:: ለአሰተዳደጋዊ ብልግናቸው ለከት ባይኖረውም የብዙዎቻችንን ደም ይቆጠቁጣል:: የተሰደቡት አቶ ሃይሉ ሻወል ብቻ ሳይሆኑ በጠቅላላው በአማራ ዘር ላይ የተነጣጠረ ዒላማ መሆኑ ነው:: በአርባ ጉጉና በሌሎችም ቦታዎች አማራ ናችሁ ተብለው እስከ ህይወታቸው እሳትና ገደል ውስጥ የተወረወሩትንና ይህንንም እልቂት ለመከላከል የተቋቋመውን የመላው አማራ ህዝብ ድርጅትን: መስራች መሪውንም ፕሮፌሰር አስራትንም ጭምር ላይ ነው የስም ማጥፋት ዘመቻው ያነጣጠረው:: ለመሆኑ አማራው ኢትዮጵያዊ አይደለምን? በፖለቲካው መስክ የመሳተፍ መብትስ የለውምን? በምን ፍርጃ ነው በአማራው ህዝብ ላይ ከወያኔ ጀምሮ ይህን ያህል የጥላቻ አታሞ የሚመታበት? ለነገሩ አንድ ፀሐፊ

«በአማራው ሕዝብ ላይ የተወረወረ ቦንብ» ያሉትን እና የኢትዮጵያን የአንድነት መሪዎች በአማራነት በመፈረጅ፣ ለአንድነት ያደረጉትን ጥረት የሚኮንነውን መርዘኛ «አማራው ከዬት ወዴት?» የሚለውን መፅሐፍ ብጤ ከፃፉት ከአቶ አንዳርጋቸው ጋር የጠበቀ ወዳጅከሆኑትና ከወያኔ የቆየ ፍቅር ካላቸው ሰው ምን ይጠበቃል!

የአቶ ክፍሌስ ከነዚህ የግም ሞት (የግንቦት) ሰባት  ዋና አስተባባሪዎች ጋር ብቅ ብቅ ሲሉ መታየታቸው ምን ውስጠ ምስጢር ሊኖረው እንደሚችል ብዙም አያስቸግርም:: አቶ ክፍሌ ለንደንን ሰለማያውቁት መንገድ መሪ ይዘው ነው እንዳንል ለዚያውም የውጭ ተወላጅ የሆኑት ባለቤታቸውና ልጆቻቸው የሚኖሩት በዚሁ ከተማ ነው::  ለሁሉም ጊዜ መልሱን ይሰጠናል:: ተሸፋፍነው ቢተኙ ገልጦ የሚያይ አምላክ አለ::